# የኢትዮጵያ የውል ሕግ ማሻሻያ ጥናት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**


አብዱራዛቅ ነስሮ

ተወዳጅ እሸቱ

ፍሬህይወት አራርሳ

ሰዊት ዘውዱ

ትዝታ ታደሰ

የምስራች ይትባረክ

1.የፍትሐ ብሔር ሕግን የማውጣት ስልጣን በሚመለከት ሕገ መንግስቱ በግልጽ ለፌዴራል መንግስቱም ሆነ ለክልሎች ሳይሰጥ በዝምታ አልፎታል፡፡ የፍትሐ ብሄር ጉዳዮች ከሆኑት መካከል የውል ሕግ አንዱ በመሆኑ አዲስ ሕግ ለማውጣት ወይም ሕጉን ለማሻሻል ሲታሰብ ይህንን ስራ ለማከናወን ስልጣን ያለው የመንግስት አካል ማን ነው? የሚለው ጥያቄ ስለ ሕጉ ዝርዝር ጉዳዮችን ከማንሳት በፊት መልስ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

2.ከውል ትርጓሜ ጋር በተገናኘ የሚሻሻለው የውል ሕግ የውልን የግዴታ ይዘት በንብረት ከመገደብ ይልቅ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ነገር (having pecuniary value) በሚል ቢሻሻል የግንኙነት አድማሱን በማስፈት ሌሎች ጉዳዮችን ማካትት ስለሚያስችል ሕጉ በዚህ አግባብ ቢቀመጥ የተሻለ ነው

3.የእድሜ ችሎታን በተመለከተ ቀድሞ እንደነበረው እና የሌሎችን ሀገራት ልምድ መሰረት ባደረገ መልኩ በፍትሐብሄር ሕግ ፣ ስለሰዎች በሚለው ክፍል ውስጥ ተካቶ ቢቀመጥ ለአጠቃቀም አመቺ ነው፡፡

4.በአሁኑ ዘመን ውል ለመዋዋል እና ለማስፈፀም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ በዋነኝነት ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ አሁን ያለውን ሕግ ከቴክኖሎጂው እድገት ጋር ማራመድ እንዲያስችል በኤሌክትሮኒክስ ለሚደረግ ውል ዕውቅና በመስጠት ሕጉን ማሻሻል ተገቢ ነው፡፡ ይህም ለንግዱ ማህበረሰብ በተለየም ለኢንቨስተሮች በአካል መገኘት ሳይጠበቅባቸው በቀላሉ እንዲዋዋሉ በማድረግ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡

5.የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚደረግ ውል በውል አዋዋይ ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ፊት ማድረጉ አስገዳጅ ባይሆን እንኳን ተዋዋይ ወገኖች ተስማምተውና ፈልገው የገቡትን ውል አልተመዘገበም በሚል ሰበብ ብቻ ውል እንዳያፈርሱ የሚገልፅ ተጨማሪ ንዑስ አንቀፅ በዚህ ድንጋጌ ስር ቢቀመጥ ቀድሞ የተመሰረቱ ውሎችን በክፉ ልቦና ተነሳስተው እንዳይፈርሱ በማድረግ ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ችግሮች

መፍትሄ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች ሊያሟሉት ስለሚገባው ፎርም አስመልክቶ ሕጉ ሲሻሻል የቀረቡትን አማራጭ ሀሳቦች በማገናዘብ እንዲሁም ሀገሪቱ ያለችበትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ታሳቢ ማድርግ ይኖርበታል፡፡

6.በአንቀጽ 1731(1) ውሎች በዋናነት ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ መሆናቸው ተቀምጦ በልዩ ሁኔታ ውሎች በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንደሚኖራቸው ከሚያስቀምጠው ምዕራፍ 7 ጋር በሚናበብ መልኩ በሕግ በተገለጸ ጊዜ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት ሊኖራቸው የሚችልበትን አግባብ ሌላ ንዑስ አንቀጽ በማስገባት ማካተት አንዱ አማራጭ ሲሆን አልያም ደግሞ በዚሁ ድንጋጌ ላይ በሕጉ (በምዕራፍ 7) ስር የተቀመጠውን በማጣቀስ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ውጤት አንደሚኖራቸው በሚገልጽ መልኩ ቢቀመጥ ተግባራዊ የአረዳድ ችግሮችን የሚፈታ ይሆናል፡፡

7.የሕግ ክፍል በመርህ ደረጃ በህጉ ክፍል 1733 የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ ሁለት በውሉ ይዘት ላይ ክርክር የተፈጠረ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ማስረጃ ማቅረብ እስከቻሉ ድረስ ውሎች ሊተረጎሙ የሚችሉባቸውን አማራጭ ሕጉ ቢያካትት የተሻለ ነው፡፡

8.በሕጉ ቁጥር 1738(1) ላይ ያለው ድንጋጌ ተግባራዊ ሲደረግ ውሉ ፍጹም አጠራጣሪ ሆኖ ለባለዕዳውም ሆነ ለባለገንዘቡም የሚጠቅሙ ሁለት አማራጮች ሲኖረውና ዳኞች ሌሎች የትርጉም ደንቦችን ሁሉ ተጠቅመው ወደየትኛው ትርጉም መሔድ እንዳለባቸው በሚቸገሩበት ጊዜ ሊሆን እንደሚገባው በሕጉ አመላካች ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

9.በሕጉ ከባለዕዳው ስልጣን ያልተሰጣቸው በሕግም በፍርድም የመፈጸም ግዴታ የሌለባቸው ሰዎች የባለዕዳውን ግዴታ ቢፈጽሙ ውጤቱ ምን አንደሆነ በሕጉ ቢገለጽ የተሻለ ነው፡፡ ህጉ ሲደነገግ ውሉን የፈጸመው ሶስተኛ ወገን በባለእዳው ላይ ስለሚኖረው የማስመለስ መብት እና ባለገንዘቡም ሁለተኛ አፈጻጸም ከባለ እዳው እንዳይቀበል ጥንቃቄ በሚኖረው ሁኔታ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

10. በውል ህጉ ላይ ሊቀመጥ የሚገባው የወለድ መጠን ባንኮች ገንዘብ ለማደር የሚወስኑትን ነው ወይስ ገንዘብ ለማስቀመጥ የሚወስኑትን የወለድ መጠን ነው የሚለውን ህግ አውጪው በጥንቃቄ አይቶ ቢወስን፡፡

11.የውል ሕጉ አንዱ ዋነኛ አላማ ውሎች እንዲፈጸሙ በማድረግ ለግንኙነቶች ጥበቃ ማድረግ በመሆኑ የሚሻሻለው ሕግ ይህንኑ በሚያረጋግጥ መልኩ ቢደነገግ የተሻለ ነው፡፡በመሆኑም ለሕጋዊ ወለድ ስሌት ገንዘቡ በጊዜው ያለውን ዋጋ ከግምት ውስጥ ማስገባትን እንደ አማራጭ ማስቀመጡ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ አልያም ከውል ውጪ ባለው የጉዳት ካሳ አከፋፈል መርህ መሰረት ካሳው ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንዲሰላ ቢደነገግ ለውሎች አፈጻጸም የተሻለ ሕጉ ጥበቃ ያደርጋል፡፡

ዳኞች ከመደበኛው ፍርድ ቤቶች ውጪ በግልግል ዳኝነት አና ሌሎች በኢ- መደበኛ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ያሉትን የሚያካትት እና ሰፊ ትርጓሜ ያለው ነው፡፡አንዲሁም በተግባር ፍርድ ቤቶች ውሎችን የሚያሻሻሉበት አስተዳደራዊ ስርዓት ስለሌላቸው የሚሻሻለው ሕግ ከርትዕ አንጻር ዳኞች በሚል ቢቀመጥ ምክንያታዊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በሕጉ የዘመድ ዳኛ ተብሎ የተገለጸው የቋንቋውን እድገት፣ ተግባራዊ ሁኔታዎችን በማገናዘብና የሚሰጠውን ትርጉም በማገናዘብ እና የሕጉን የአንግሊዘኛ ትርጉም በመውሰድ የግልግል ዳኛ (Arbitrator) በሚለው ቢተካ የተሻለ ትርጉም ይሰጣል፡፡

12.ሕግ አውጪው ውል ሳይፈጸም ሲቀር እና ኪሳራ ሲኖር በውላቸው የመቀጫ ስምምነት ያስቀመጡ እንደሆነ የጉዳት ኪሳራ እና የመቀጫ ስምምነቱ ስለሚፈጸምበት አግባብ በሕጉ በግልጽ ቢካተት፡፡

13.ከቁጥር 1808 እስከ 1813 ድረስ ባሉት የአማርኛው ድንጋጌዎች “invalidation” የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል “የውል መሰረዝ” ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ይህ ደግሞ “cancellation” የሚለውን ቃል የሚተካ እንጂ ውል ማፍረስ “invalidation” የሚለውን ቃል የሚተካ ትርጉም አይደለም፡፡ ውል ማፍረስ “invalidation” እና ውል መሰረዝ “cancellation” የተለያየ ምክንያትና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ሀሳቦች ናቸው፡፡ እነዚህ አንቀጾች የውል መፍረስን ፅንሰ ሀሳብ የሚገልጹ መሆናቸውን ከሕጉ የእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር በማገናዘብ መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በእነዚህ ድንጋጌዎች ውስጥ ያሉት ውል እንዲሰረዝ የሚሉት አነጋገሮች “invalidation” በሚለው የእንግሊዘኛ ቃል መተርጎማቸው ስህተት በመሆኑ ውል እንዲፈርስ በሚለው ሐረግ ሊተኩ ይገባል፡፡በፍሬ ሀሳብ ረገድ ሕጉ ፈራሽ እና ዋጋ አልባ ውሎች ምንነት እንዲሁም ምን አይነት ሁኔታ ሲኖር ፈራሽ (voidable) ወይም ዋጋ አልባ (void) እንደሚሆኑ ተካትቶ ቢቀመጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን ውዥንብር በማጥራት ሕጉ የተሻለ ግልፅነት ይኖረዋል፡፡

14.በተለየ አኳኃን የተደረገ ውልን ለማሻሻል የተለየ ፎርም እንደሚያስፈልገው ሁሉ በተለየ ሁኔታ የተደረገ ግዴታ በአዲስ ግዴታ ለመተካት የተለየ ፎርም ተከትሎ እንዲደርግ ግልፅ ድንጋጌ ቢኖር የተሻለ ነው፡፡

15. በንፅፅር የእኛን ሕግ ስንመለከት የተቀመጡት ምክንያቶች ውስንነት የሚታይባቸው እና በሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሕጉ የተሟላ እንዲሆን ሌሎች የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶችን በካተተ መልኩ ቢሻሻል ተመራጭ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ የሰፈረውን የይርጋ ድንጋጌዎች ተከሳሽ ወገን ካላነሳው ፍ/ቤቱ በራሱ ሊያነሳ እንደማይችል በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1856 የተጠቀሰ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው ለይርጋ ድንጋጌዎች እንጂ በሕግ ግምት የማስረዳት ሸክም ከአንድ ወገን ወደሌላው በሚዘዋወርባቸው ሁኔታዎች አለመሆኑን አመላክቷል፡፡ በመሆኑም የይርጋ ድንጋጌዎችን ከሕግ ግምት ድንጋጌዎች ጋር ማመሳሰል የህጉን መንፈስ፣ አላማና ግልጽ ይዘት ያልተከተለ መሆኑን ገልፆ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በዚሕ ረገድም በሁለቱ መካከል ስላለው ልዩነት በግልጽ በሕጉ ላይ ቢቀመጥ አሁን ያለውን ችግር ሊፈታ ይችላል፡፡